# ደርሶባችሁ ይሆን እናንተም እንደኔ!!!
# እውን ኢ.ሕአፓ መሆን ያኮራል?

ከቤልጅግ አሊ

- ስለ አንድ ጎበዝ የተሳካለት ሰው ጠይቃችሁ ።እሱማ የድሮ ኢ.ሕአፓ ነው ። ይህም ሲያንሰው ተብላችሁ።
- እከሌ ጥሩ መፀሐፍ ፃፈ !! በአሁኑ አደል በድሮው እውቀቱ ነው።ድሮ ኢ.ሕአፓ ነው አሉ ።
- እከሌ ጥሩ ትዳር አለው ። እንዴ ባለቤቱ እኮ ኢ.ሕአፓ ነች አሉ።
- እከሌ ዶክተር ሆነ !! እሰካሁን ምን ሆኖ !! ስብሰባ ላይ ሲናገር የበሰለ ነው።እሱማ ድሮ ኢ.ሕአፓ ሰለ ነበር ነው።
- እከሌ ቆራጥ ታጋይ ነው !! ኢ.ሕአፓ መሆኑ ቀረ!!
- እከሌ ጥሩ ገጣሚ ነው !! ኢ.ሕአፓ ነው ከርቸሌ አውቀዋለሁ !!
- በዚህ ደራሲ ነው ! በዚህ ገጣሚ ነው ! በሁሉም ችሎታ አለው ።እድሜ ልኩን ኢ.ሕአፓ መሆኑ ቀረ!!!
- አየኸው እስብሰባው መሀል የተቀመጠው?የበሰለ አሳብነው የሚያቀርበው ።የኢ.ሕአፓ ከፍተኛ አመራር ነው ።ታዲያ እታች ከህዝብ ጋር ምን ይሰራል?እነርሱን ተውቃቸው የለ እንዲህ ናቸው ።መች እዩኝ እዩን ማለት ይወዳሉና።

እንደዚህ አይነት አባባሎች ብዙ ጊዜ ይገጥሙኛል። ምናልባት እናንተም እንደኔው ደርሶባችሁ ይሆናል ። ከኢ.ሕአፓ ድሎች ውስጥ ብናስመዘግባቸው ይቻል እንደሆን አላውቅም ። ህዝቡ ለፓርቲው የሰጠው አመለካከት ነውና በተቀነባበረ ቅስቀሳ እንኳን ሊፋቅ አልተቻለም ። አንዳንዴ እንደዚህ አይነት አባባሎች አይናችውን ቀይ የሚያደርግባቸው አይጠፉም ። ይታደሉታል እንጂ ገርፈው እንደማያገኙት እርግጠኛ ነኝ ። ታሪክ በህዝብ ይፃፋል ማለት ይህ ነው ። ታሪክ በገዥዎች ቢፃፍ ኖሮ እስከ አንድ ሰው ሲቀር ድረስ እንዋጋለን ብለው ቀድመው ታሪካቸውን የፃፉት ሁሉ፡ያ እንደውነት ተቆጥሮ በተነገረላቸው ነበር ። እሱ አገሩን ይወዳል የሚለው መፈክር ከፕሮፖጋንዳነት አላለፈም ። ቆራጡ መሪ ቆርጦ ከመፈርጠጥ በላይ ያሳየው የቴዎድሮስ ወኔ የለም። አሁንም ደግሞ ተደጋግሞ ያንን የሆዳሞች ስብስብ መንግሰት በፕሮፖጋንዳ ለመካስ የሚደረገው ጥረት የተሳካ አልሆነም ። ስለዚህ የኛ ስም ከጠፋ የነርሱስ ለምን ይቅር የሚለው የጅቦች መፈክር ተደጋግሞ በፀረ ወያኔ ትግል ውስጥ ብቅ ሲል እናየዋለን ። እነርሱን ተዋቸው ኢ.ሕአፓዎች ናቸው። ለዘላለም አይለወጡም፡ የሚለውንን አነጋገር በሰልን ከሚሉ ፖለቲከኞች ጭምር እንሰማዋለን። ያልገባቸው ነገር ቢኖር የማይለወጠው የተነሳንበት አላማችን እንደሆን ነው። አንድ ፆታውን መቀየር የለመደ ሰው ፤ በአንድ ፆታ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚቻል መስሎ አይታየውም ። ይባስ ብሎ በፆታው መቆየት የቻለውን ሁሉ ጭፍን ድንብሩን ቢሳደብ ሊደንቀን አይገባም ።

ከዚህ በታች ያለውን ታሪክ ያጫወቱኝ በአሁኑ ጊዜ በሕይወት የሉም ። የጓደኛዬ እናት ናችው ። ከአዲስ አበባ ሴት ልጃችውን ሊጠይቁ መጥተው ሰለ ኤድስ ብጠይቃቸው ያሉኝ መልሰ እስከአሁን ያስደንቀኛል። ፅሁፋን ለእሳቸው መታሰቢያነት እሰጣለሁ ። ሰው ነኝና ያስቀየምኳቸው ካለ በዚሁ ይቅርታዬን እጠይቃለሁ።

- ይህ በሽታ በእናንተ ጊዜ ቢሆን የሚሞተው ሰው በጣም ያንስ ነበር ።

- ለምን እናቴ?
- በእናንተ ጊዜ የነበራችሁት ወጣቶች ኢ.አባ ስለሆናችሁ።
- ከሱ ጋር ምን አገናኘው ?
- አይ ልጄ ምንስ አለያይቶት?
- አልገናኝ ቢለኝ?
- አስበው እንጂ። አንተ እነርሱን አልነበርክ? እናንተ ለመሆኑ ከቁምነገር በቀር ለሌላው መቼ ቦታ ሰጥታችሁት? እናንተ ለሰው ችግር ብላችሁ መሞት እንጂ ፡ ለራሳችሁ መች ሞታችሁ ታውቃላችሁ ። ይህ በሽታ ያኔ ቢሆን አንዳችሁንም አይነካችሁም ነበር።
- አይ እማማ እኔ እንደሱ አላየሁትም ነበር።
- እኔም እዛ ሰፈር አሮጊቶቹ ስንሰበሰብ የምናወራውን ነው እንጂ። መቼስ እኔ አልተማርኩ ከየት አምጥቼው? እኔ ከእናንተ የበለጠ አላውቅ። ሴቶቹ የሰፈሩ እነርሱ ካልመጡ ይህንን የመጣብንን መአት የሚያነሳልን የለም ነው የሚሉት።
- ምኑን ኤድስን ?
- ወያኔን ነው እንጂ ፡ ይህንን የቀትር ሰይጣንን ።
- እሱንማ ይኸው ብዙዎች እየታገሉት አደል ?
- ከቴም ትግል ፡ ውስኪ አብሮ እየተጠጣ ። ሻንፓኝ በየኤንባሲው እየተቀዳ ፡ ማታ ህዝብ እየተረሳን ፡ጠዋት እየታወስን ። ተወኝ ልጄ ፡ ትግል መቼስ ካልመረረ ፤ ትግሉ መቼ ትግል አይሆን። በእንደዚህ አይነት የነርሱን መውረድ እኔ እንደተመኘሁት አላየውም ማለት ነው። ያኔ በቀይ ሽብር በራፋችን ላይ ደርግ እየገደለ የሚጥላቸው ፡ውስኪ መጠጣት አቅቶአቸው መሰለህ ። ለደሃው ለተበደለው ፡ መሬት ለሌለው ፡ ለጭሰኛው ፡ ለገበሬው ፡ ለሰራተኛው ለተጎሳቆለው ብለው ነው።ቀንም ሌትም ሳይረሱን፡ለኛው ነው የሞቱልን፡፡ እንዲያውም ከፈለግህ የሰፈሩ ሰው የሚለው የአሁኑንን ወጣቶች በደርግ ጊዜ ቢያደርጋቸው ኑሮ ፡ ከደርግ ተስማምተው አገሪቱዋን ሽጠው፡ ቢሰነስ ይሰሩባት ነበር ።
- ቢስንስ ደሞ ምንድነው ?
- ይህን አተኸው ነው? ንግድ ነዋ ። እናንተን ደግሞ አሁን ነበር ማግኘት ። ይህንን በውሸት የተሞላ መንግሰት ፤ በወረቀቱም በምኑም ታጋልጡት ነበር ። ያሁኑ ወጣትማ እናንተ ላይ የደረሰውን እየሰማ „ሞኝ ያለቀው በቀይ ሽብር“ እያለ እንዲቀመጥ አርገውት ። በጋዜጣው ላይ ለአገሩ የሞተውንን እየሰደቡ እየፃፉ አስፈራሩት።እሄው በሽታውን ታቅፎ ቀረ። ሞት ላይቀር ። ገለባ ሞት ሞተ ።
- መቼም ሚች እራሱን ጎዳ።
- ቢሞትስ ልጄ የከበረ ሞት ።

“ምነው ጥቁር ለበሱ“

„ልጅ ሞቶብኝ „

„በምን?

„ በቀይ ሽብር „

-ማለት ደስ ሲል ባየኸው።

-የዘንድሮ ታዲያ አፍረቱ በምን እንደሞተ ለመናገር ። አይጣልብህ፡

- በሽታው ፍለጋው፡
- በኤድስ እንዳይመሰል። የሞተው በሌላ በሽታ እንዲመስል። መስሎን ነው እንጂ ያልደረሰበት አለ ብለህ? ሁሉም ያውቀዋል ።

- ቀብር ሄደን አንዲት አልቃሽ ባለፈው ምን እንዳለች ታውቃለህ ።ለዚህኛው የሚያለቅስ ብታጣ። ሰው ሞት በዝቶበት።

አትቆጪኝ እንደሁ አዲስ ባለ ሬሳ
የቀይ ሽብሩንም ሰላባ ባነሳ ።
ያኔ በቀይ ሽበር መሃል ያየሁህ
ሀዘን ዕጣህ ሆኖ ዛሬም እዛው ነህ።

የልጅሽ አድራሻ አስሰሽ ያጣሽ
እስቲ እህ በይኝ እኔ ልንገርሽ
በጅምላ ረሸኖ ጉድጓድ ጣለልሽ
መርዶም አትጠብቂ ዛሬ ላላቅስሽ።

ሰትል ያልቀበረው ሁሉ አልቅሶ ሊሞት። ፊት በቀይ ሽብር የሞቱትን የሰፈር ልጆች አንስታ ስታስለቅሰን ዋልን ።ልጄ የከበረ ሞትም አለ ። የገንዘብ ብቻ አደለም ሃብት ።

- ስለጓደኛዬ መጠየቅ ብፈልግም ስፈራ ስቸር እሱስ እንዴት ነው አልኩዋቸው?
- እሱማ ምን ይሆናል ብለህ ። ለአስራ ሰባት አመት ስደት ከርሞ፡እኛ እንኳ ሳናገኘው ከርመን ፤ ደርግ ከወረደ በሆላ አንድ ቀን ብቅ ቢል እተቀመጥኩበት ውሃ ሆኜ ቀረው ።
- ሁላችንም እኮ መርዶውን ሰምተን አልቅሰን ነበር?
- መርዶውማ የአንተ አባት አሳብ ነው እኮ ።አላወቅህም ነበር?
- እንዴት ? አባቴ ለኔ ምን የሰው ሚስጥር ይነግረኛል ብለው ።
- እሱማ እውነት ነው ። ለዚህ አደል የሰፈሩ ትልቅ ሰው የተባሉት ። መቃብራቸው ላይ ቄሱ እኮ ያሉት እውን ነው ።

"የደብራችንን ሰው ሆይ ከእንግዲህ እንዳትጣላ፤
የሚያስታርቅህ የለም ፤
እንዳትሞት የሚገንዝህ የለም ፤
እንዳትቸገር የሚያማክርህ የለም ነው ያሉት"።

ወደ ሶሰት ሺህ ሰው ነው የቀበራቸው ።እኛማ አብረን ኖረን ተዛምደናል ። እንኳን ለኛ ለመጤውም አባት ነበሩ ።

- ታድያ መርዶው ምንድ ነበር ?
- እሱማ! ቀበሌ ወስደው እናንተን እሱን አምጡ ብለው ከሚያሰቃዩአችሁ እኔ መጥቼ የሆነ ይሁን ብሎ መልክተኛ ይልክብናል።
- ማን ?
- ጓደኛህ ነዋ።
- የምናደርገው ቢጠፋ ለእርሳቸው ለመንገር እንሄዳለን ። በይ አንቺ ሂጂ ብለው እኔን ያሰናብቱኛል ። ጉዱን አላወቅሁ ወደቤት ተመለስኩ ። ሁለቱ ወንዶች ተነጋግረው ጨርሰው፡ ለካ ምስክር ያየ ስለሚአሰፈልግ ፡ ሌላ አባትህ የሚያውቁት የታመኑ ሁለት ሽማግሌዎች ምስክር ሆነው፡ በቀይ ሽብር ተመቶ ወድቆ እንዳዩት ሆኖ ቅዳሜ ለት አረዱኝ ። እኔም እዬዬ ብዬ እርሜን አወጣሁ ።እድርም በላሁበት ። አሁን ደርግ ሲወርድ ነው ገንዘቡን የመለስኩ ። ቀበሌም ፍለጋውን አቆመ ። እነዛ ሽማግሌዎች በዚህ አይነት ብዙ ሰው አድነዋል አሉ ። የኔም ባለቤት በሌላው ምስክርነት ቆመው ይሆናላ ። አየሽው ቄሱ ያሉት እውነት ነው ።እኛም ከግርፍ ዳንን እሱም ከሞት ተረፈ።
- ከዛስ ?
- አንድ ቀን ምሳ አባትህ እኛ ቤት ተጠርተው ሳለ ። በይ እንግዲህ እውነቱ እንዲህ ነው ብለው አስጠንቅቀው ነገሩኝ ። እስከማየው ግን አላመንኩም ነበር፡፡

በድብቅ ተምሮ ዩኒቨርሲት ጨረስ ። መቼስ ጎበዝ አደል የድሮ ኢሕአፓ ። ችግርን ፉት አላት ። ተመስገን ነው አሁን ለሶስት የልጅ ልጅ አብቅቶኛል ።

- እንደው ወደዚህ ሲመጡ ምንም አላከም ? ደብዳቤስ ቢሆን ?
- እንደው ሁል ጊዜ ይገርመኛል ፡ምን ሰይጣን እንደገባ በመካከላችሁ? ፍቅራችሁ ስለሚበዛ ጠባችሁም ይከራል ። ፃፍለት ብለው፤ ወቅቱ አደለም አለኝ ። ሌላም አለልኩት፡ አይኑ ደም ሲመስልበኝ ተውኩት ።ያስቀየምከው ካለ አንተው ፃፍለት ። በግል ግን እንዳላስቀየምከው አንገቴን እሰጣለሁ ።እሱም የግል አደለም ነው የሚል ። እናትህን ያን ሰሞን ላመትባል መጥቶ እቤት ስላልነበሩ ሲጠብቃቸው ፎቶህን እያየ ሲያለቅስ ደረሱበት ። ግራ ቢገባቸው እኔን ጠየቁኝ ። አይ ብንተዋቸው ይሻላል አልኳቸውና ተውነው ። በአለፈው የላክለትን የይሁዳውያንና የጀርመኖችን የሚገልፀውን መፅሐፍ ጠርዞ አስቀምጦታል ። የኛን ታሪክ ነው የሚመስለው ነው የሚለኝ።ታሪካቸው እንደኛ ያኮራል ነው የሚለኝ።

- ለመሆኑ እማማ ኢሕአፓ መሆን ያኮራል?
- እንዴት አያኮራ ልጄ ። ያኮራል እንጂ ። እንኳን መሆን እራሱን ኢአባን፤ የነርሱም ወላጅ መሆን ሲያኮራ ። ወያኔ የገባ ግዜ አንተ እዚህ ሆነህ አላየኸውም እንጂ ፡ የሰፈሩ አደዝዳዥ ሁሉ ኢአባ ነበርኩ ነው ያለ ። ጥቅም የሚገኝ መስሎአቸው። ያ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ የቀበሌ አብዮት ጥበቃ የሴት ቀሚስ ለብሶ ሲሮጥ ባየኸው ።ሲያስጠላ ወንድ ልጅ እንዲህ ጡርቂ ሆኖ ሲፈጠር ።ምነው በናታቸው መሀፀን ደም ሆነው በቀሩ ኖሮ ።

> ሲለፈልፉ ከርመው ፡፡
> እስከመጨረሻው ሲሉ ከርመው ።
> እሰከ አንድ ሰው ሲቀር ሲሉ ከርመው ።
> የቁርጡ ቀን ልጅ ነን ሲሉን ከርመው ።

ለነዚህ ጥለውን ይሂዱ ።እርስ በርሳቸው ነው እኮ እየተጠቋቆሙ የተያዙት ።

> -ወያኔ ደግሞ ምኗ ዋዛ ፡
> -ያኔ የበላኸውን ጉቦ ክፈል ብላ ማነቅ ።
> -ከየደበቁበት ነው አምጥተው የመለሱት ።

እነዚህን ከመሆን የሞቱትን ኢአባዎች መሆን ይሻላል።ስማችው ከመቃብራቸው በላይ የተፃፈው።ኸርግና ነው የተባሉ ።

- ለመሆኑ የሰፈሩ ሰው እንዴት ነው ?
- ተጎዳ በረሃቡ ፤ በበሽታው ፡ በሃዘኑ ፤ ተደራረበበት ፤እግዚሄር ምህረቱን አራዘመው ፡ዘመድ ውጭ ያለው እንጂ ሌላው መች ችሎት ። በሞቴ አንድ ነገር ላጫውትህ ?
- ምን ገዶኝ እናቴ ።
- እኛ ከእናንተ ቤት በላይ ያሉተን ጠላ ነጋዴ መቼም አትረሳቸውም ። አሁን በቅርብ አረፉ። ነፍሳቸውን ይማረው ።እዛ ጎረቤት መርዶ ነበር ። የቆንጆትና የሃዳስ ቀልድ ሳይጀመር አንድ ነገር አጫውተውን ስንስቅ አመሸን ። ያ ከናንተ ቤት በታች የነበረው ጥርስ ወላቃው ፤አንድ ሰሞን ካድሬ ሆንኩ ብሎ ሰፈሩን ያምስ ነበር ። ታድያ የሸማግሌውን ልጅ ፤የጡረተኛው ጎረቤታችሁ ፡የባሻን አንድ ልጅ፡ ታውቃቸው የል ?
- እንዴታ አውቃለሁ እንጂ ።ጓደኞችን አልነበር ።

- አዎ ነበር እንጂ ።ታዲያ እሱን ሊያስር ሲመጣ፤አይተውት ኖሮ እሳቸው ሲጮሁ ሰፈሩ ወጥቶ ጮሆ አዳነው ። ታዲያ ካድሬው ይህችንን ቂም ይዞ ጠላ ሻጭዋን ያኔ አስሩዋቸው ትንሽም ገርፎአቸው ነበር ።

- እሺ እባኮት ።

- ደርግ የወረደ ቀን ደጅ ተቀምጠው ጥሬ ሲለቅሙ ሳል፤ ካድሬው እቃውን ጠቅልሎ ሲሮጥ ያዩትን ጊዜ።

„አሁን ወዴት ይመለጣል ብለህ! አንተንም ሊይዙህ ቢመጡ ደግሞ መጮሂና መታሰሬ  አይቀር“

ብዬ አልኩት ብለው ስንስቅ አመሸን ።
የማጋለጡ ላይ ህዝቡን ይቅርታ ጠየቀ ። ህዝቡም ለልጆቹ ተብሎ፤ በዚያም ለነዚህ ሰይጣኖች አሳልፈን አንሰጥም ተብሎ ተለለቀ ።። እንደሰማሁት ሌሊቱን ሲጮህ ነበር  የሚያደር ። አሁን እራሱን አጠፋ ።የሰው ደም መርዝ አደል መች እንዲህ በቀላሉ ይለቅ ብልህ ።

- ታድያ የሃዳስና የቆንጅት ነገር እንዴት ሆነ?
- የሃዳስ ነገርንማ አንጀታችን ውስጥ ገብቶ ቀረ።ወያኔ ሲገባ ስትሳደብ ፤ተይ እነዚህ ሰዎች ቂመኞች ናቸው ስንላት፤ እንቢ ስትል ። ቀን ጠብቀው የባድሜ ጦርነት ሲጀመር በሌሊት መጥተው ፤በጠፍ ጨረቃ ከተኛችበት በሌት ከነልጆቹዋ ወደ አስመራ አባረርዋት። እስዋም ሆነች ልጆቹዋ አስመራን መልመድ አቅትዋቸው ሲሰቃዩ ከርመው፤ አሚቼ እያሉ ሲሰድቡዋቸው ፤ ከዛ የሸሹ መስሎዋቸው፤እራሳቸውን በጥሩ ኤርትራነት ያስመሰከሩ መስሎዋቸው፤ አስመላሽ ሰዋ ሄዶ መመዝገብ ። ኢሳያስ ለአሚቼዎቹ ጉዳዩም አደል የሚባል፤ አምጥቶ ባድሜ ላይ የቦንብ ማብረጃ አደረጋቸው ። የቆንጂት ልጅ ማሙሽም ተው ባድሜ አደለም ድንበርህ ብንለው አልሰማም ብሎ በወያኔ ተመልምሎ ፡ እሱም የመሃል አገር ሰው ስለሆን ለወያኔ ምንም ሳይሰማው የቦንብ ማብረጃ ሆነው ቀሩ ። ሰፈራችንን ሃዘን ዋጠው ። የድሮ ሰውም አይታይም ። መጤ ነው የበዛው ። ለመሆኑ አንድ ነገር ልጠይቅህ በሞቴ ። ለዛ ለካድሬ ገንዘብ እረዳኸው የሚሉት እውነት ነው ?
- ምን ላድርግ ብለው ተቸገርኩ እራበኝ ቢለኝ ።
- ያንን ሁሉ አድርጎህ ? ገርፎህ ? ጓደኞችህን ገርፎ ፤ገሎ ፤ አሁንስ ልጠላህ ነው ልጄ !!
- ተራብኩ ቢለኝ ፤ታረዝኩ ፤ልጆቼ እራባቸው ቢለኝ ፤ የማውቀው የለም ቢለኝ የሚረዳኝ ፤ ያለኝን አውጥቼ እረዳሁት ፤ የኔታ ጀማነህን እረሱዋቸው የቄስ አስተማሪያችንን ፤ያሉን እኮ "ክፉ የሰራብህን ደግ ስራለት ነው" ።  ኑዛዜዬ ነው ብሎ ፤ ለሰው እንዳትነግር ብሎ ፤ የደበቀውን ታሪኩን ፅፎ ፤ ስሞት አውጣው ብሎ ላከብኝ ። አነበብኩት ፤አነበብኩት ፤ አነበብኩት ፤እንዴት ያሳዝናል መሰሎት ።

ሰው እንዲህ ጨካኝ ሆኖ ሲፈጠር
የጋህነብ እሳት ካቦ ሆኖ መኖር
ሌላውንን አውርዶ አንዱን ሰቅሎ
ብረት በሰው ሰጋ ውስጥ ዶሎ
ገሎ መልሶ ፎከሮ
ቀን ሲያልፍ እንዲህ አፍሮ
እረ ይተውኝ እናቴ
ምንስ ተብሎ ይነገራል።

- አውቆታል ኢሕአፓ መሆንህንን ፤ በሰው እንደማትጨክንን ፤ ጓዶቹን ትቶ፤ አንተ ጋ መምጣቱ መማሩ አደል ፤ ጥፋቱ ቢገባው፤ይሁንና ሌሎቻችንስ ብናውቀው ኑዛዜውን ። እሱ እንደሆን አርፎአል ።

- የመጨረሻው ደብዳቤ በደረሰኝ ጊዜ ደውልልኝ ስላላ ብደውልለት በል እንግዲህ ደህና ሁን ። የልጆቼን ነገር አደራ አለኝ ። እኔም የተሻለኝን አደርጋለሁ ብዬ ቃል ገባሁለት ። መች መስሎኝ የመጨረሻ ቃሉን የምሰማ ። በሌሊቱ እራሱን አጠፋ ። መቼም አይገባም ነበር እራስን ማጥፋት ። እንደገና በሰማይ ቤት መኮነን ።
- እኛም ሰምተነዋል ጭምጭምታውንን ። ለቅሶ ቤት ተነስቶ ሲወራ ። ሁሉም መጀመሪያ አንተ እረግመውህ ነበር ። በሆላ ለልጆቹ ሲል ነው፤ ሲባል ጊዜ ።ሁሉም ድሮስ ኢአባ አደል ነው ያሉት ። ይባርክህ ልጄ ፡፡ በልጅነትህ የተሰቃየኸውን ቆጥሮ ለዘላላም ብሩህ አለም ይስጥህ ፤ አትዘን ፤ ልጆችህ ደስተኞች ይሁኑ ። ሰው በጠፋበት ዘመን በስተረጅናዬ ለህይወቴ ተስፋ የሚሰጠኝ ነገር መስማቴ ። አለም ተበላሽታለች ብዬ በማስብበት ጊዜ ይህንን ማወቄ ። በመቃብሬ ላይ የቆምኩ ነኝና ስላገሬ የወደፊት ሁኔታ ሳስብ እናንተ አሁንም ከበጎ ተግባራችሁ ጋር መኖራችሁን ማወቄ ። በመጨረሻው የሞሞቻዬን ቀን አጣፈጥክልኝ ። ተስፋ መገብከኝ ። ከአሁን ወዲያ ከሆዳሞቹ ባሻገር ጥሩ ሰዎች እንዳሉ ስላወቅሁ አፈሩ ቀለል ይለኝ ይሆናል ።

በሉእስቲ በሰላም ይክረሙ ። እየተመላለስኩ እጠይቃለሁ ብዬ ተለያየን ።
ማምሻም እድሜ ነች ።በርታ አሉኝ።
እስቲ ስለኛ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይክረም !!

ቤልጅግ አሊ

ይቀጥላል።